# የኢሳፕ ዜና መጽሔት ESAP FLASH

ቅፅ 3 / Issue 3 መጋቢት 2006 / March, 2014

ውድ አንባቢያን



የኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም (ኢሳፐ 2) የስራ አመራር ኤጀንሲ በማህበራዊ ተጠያቂነት ዙሪያ ከመስክ ጉዞና ከዋና መሥሪያ ቤቱ በተገኙ ዘገባዎች ላይ ተመርኩዞ ይህን 3ኛ ዙር የዜና ጥንቅር ሲያቀርብላችሁ ታላቅ ኩራት ይሰማዋል። በዚህች እትም ከተከበሩ ዶ/ር አብርሃም ተከሰተ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታና የማህበራዊ ተጠያቂነት ጥምር ኮሚቴ ስብሳቢ ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ ይዘን ቀርበናል። ሰብሳቢው በፕሮግራሙ ዙሪያ ብሎም በኢትዮጵያ ያለውን ተግባራዊነት በተመለከተ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ከዚህም በላይ የዜና ጥንቅሩ ባለፈው የካቲት ወር በአዳማ ከተማ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራምን የሚተገብሩ 49 ድርጅቶች የተሳተፉበትና ልምዳቸውን የተለዋወጡበትን አውደ ጥናት ይዳስሳል።

አውደ ጥናቱ የተዘጋጀው በድርጅቶች መካከል የልምድ ልውውጥ ለማድረግና የፕሮጀክት ትግበራ ሂደትን ለማፋጠን ነው። በአውደ ጥናቱ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራምን የሚተገብሩ 49 ድርጅቶች ባለሙያዎች፣ ከፌዴራል የክልልና የከተማ መስተዳደር ተወካዮች፣ ለጋሾችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሣታፊ በመሆናቸው መድረኩን የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ረድቶታል።

የመረጃ ስርጭትን በተመለከተ የኢሳፐ 2 የስራ አመራር ኤጀንሲ በአሳታፊ ቪዲዮ ዶክሜንቴሽን ዙሪያ ሁለት ዙር የስልጠና መድርኮችን አዘጋጅቶ ነበር። በነዚህም የስልጠና መድረኮች ከፈፃሚ ድርጅቶች የተውጣጡ ተሳታፊዎች በማህበራዊ ተጠያቂነት ዙሪያ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ባለድርሻ አከላትን በማሣተፍ አጫጭር የቪዲዮ ፊልም ቀረፃዎች እንዴት እንደሚካሄዱ ልምድ እንዲቀስሙ ተደርገዋል። እነዚህ አጫጭር የቪዲዮ ዶክሜንቴሽን ሥራዎች ሰፊ ሽፋን ያለው የልምድ ልውውጥን ተግባራዊ ለማድረግ አይነተኛ መማሪያዎች መሆናቸው ታምኖበታል። በኢሳፐ 2 ድረ ገጽ ላይ የተሰራጨው መረጃና ብሎም በፌስ ቡክ ገፃችን እየጨመረ የመጣው ተመልካች የማህበራዊ ተጠያቂነት ጉዳይ አሁንም በኢትዮጵያ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው የሚለውን ዕምነታችንን የበለጠ እንዲጐለብት ረድቶታል።

መልካም ንባብ

ሮልፍ ሁኒንክ
ኢሳፐ 2 ቡድን መሪ

*Dear Reader,*

*The ESAP2 MA is proud to submit its third Newsflash with a wide range of interesting stories both from the field and from headquarters highlighting Social Accountability. In this newsletter you will find an interview with Dr. Abraham Tekeste, the State Minister of Finance and Economic Development, who also chairs the Social Accountability Steering Committee. He sheds light on aspects of Social Accountability in general and how it is applied in Ethiopia today.*

*The Newsflash also provides an overview of the successfully organized benchmark sessions in Adama in February when all 49 SAIPs were invited and encouraged to exchange views and field experiences. The benchmark was meant to be a learning exercise and should ideally result in an acceleration of project implementation by our partners. Apart from the 49 SAIPs, federal and regional government officials as well as donor and related program representatives also attended the sessions, made it even more valuable.*

*With regard to the distribution of information, the MA organized two separate training sessions on Participatory Video Documentation. SAIP staff learned how to shoot brief videos in which attention was addressed to stakeholders involved in Social Accountability at Woreda and Kebele level. These video productions are considered to be a strong mechanism for experience sharing with a wide coverage. The information published on the ESAP2 Website as well as the increasing number of 'likes' on Facebook strengthens our belief that Social Accountability in Ethiopia is a lively subject.*

*Happy reading!*

*Rolf Hunink*
*ESAP2 team leader*

## እኔ ተጠያቂ ነኝ እርስዎስ ?

እኔ ተጠያቂ ነኝ እርስዎስ ? የሚለው የኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም (ኢሳፐ2) የወቅቱ መሪ ቃል ነው። መሪ ቃሉን በስቲከሮች ላይ በማተም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ተደርጓል። ይህ መሪ ቃል በድረ ገፃችንና በፌስ ቡክ አድራሻችን ላይም በጉልህ በሚነበብ መልኩ ይገኛል። በዚህ አጋጣሚ መሪ ቃሉን በተመለከተ ሃሳባቸውን ላጋሩን አካላት ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን። ለመሪ ቃሉ ምርጫ የተደረገው ውድድር በአለም አበበ አሸናፊነት የተጠናቀቀ ሲሆን በዚህ አጋጣሚ አሸናፊዋ እንድታነጋግረንና ለዚህ ውድድር የተዘጋጅውን ሽልማትም ትቀበልን ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን።

## I am accountable, are you?

*I am Accountable, are You? Is the new slogan for the second phase of Ethiopia's Social Accountability Program (ESAP2). The slogan is printed on stickers that are handed out to all involved stakeholders. The slogan can also be found on our Website and Facebook.*

*We would like to thank everybody that sent in ideas for the slogan. AlemAbebe won the slogan competition. We kindly ask Alem to contact us so we can make sure to reward her.*

# ዜና News

## የመስክ ዘገባዎች

በጥር ወር በኤጀሬ ወረዳ የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያ በሆነው በማህበረሰብ ውጤት ካርድ ዙሪያ በተደረገ ውይይት ወቅት ተሳታፊ የነበረች አንድ ወይዘሮ የሁላችንንም ልብ የነካ ልምዷን አካፍላን ነበር ።

ወይዘሮዋ ካላት አነስተኛ ገቢ አኳያ ራሷንም ሆነ ልብሶቿን አጥባ እንደማታውቅ ነበር ያጫወተችን። ከዚያም ባለፈ ወደ ጤና ጣቢያ በምትሄድበትም ወቅት ሌሎች ሰዎች ንፁህ ለብሰው እንደምታይና እንደዛም ስለሆኑ ብቻ ከሷ ቀድመው የጤና አገልግሎት ሲሰጣቸው እንደምታይ ነው በሃዘን የገለፀችልን። የጤና አገልግሎት ባለሞያዎች እሷን በማቆየት ሌሎችን ሲያስቀድሙ ሁሌም ብታይም ያን የተለመደ ነገር አድርጋ ትውስድ እንደነበር ነው ያጫወተችን።

አሁን ግን በኦሮሚያ ራስ አገዝ ድርጅት (OSHO) እና የሴቶች ድጋፍ ማህበር (WSA) የተዘጋጀው ስልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ምስጋና ይግባውና እንደማንኛውም ግለሰብ በተራዋ ና እንዳመጣጧ በጤና ተቋሙ የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ከማንኛውም ሰው እኩል የማግኘት መብት እንዳላት መረዳት ችላለች።



## የአካባቢ መሥተዳደሮችና ማህበረሰቡ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል በአካባቢው የሚገኘውን ሀብት ማሰባሰብ ቻሉ

የአማራ ልማት ማህበር በስፋት ከሚንቀሳቀስባቸው ከተሞች አንዱ በሆነው በደብረ ማርቆስ የመፀዳጃ ቤቶች እጥረት፣ አገልግሎት መሥጠት ያቋረጡ ቤተመፃህፍት፣ የመምህራንና የተማሪዎች የመማሪያ መፃህፍት እጥረት፣ ለችግር የተጋለጡ ህፃናት በከፍተኛ መጠን ትምህርታቸውን ማቋረጥና የመሳሰሉት ትምህርት ነክ እና ተያያዥ ማህበረዊ ችግሮች በሰፊው ተሰተውሏል። እነዚህን ከፍተቶች ለመቅረፍ በወረዳው በተደረገው የገፅ ለገፅ ውይይት ወቅት የህዝብና የመንግስት ተወካዮች እንዲሁም አገልግሎት ሰጪ አካላት በመወያየት የጋራ የድርጊት መርሃ ግብር በመንደፍ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅትም የከተማ መስተዳድሩ ለመፀዳጃ ቤቶች ግንባታ የ22 ሺህ ብር ለመመደብ ችሏል።

## ማህበራዊ ተጠያቂነት ዙሪያ የሚያጠነጥን ዘጋቢ ፊልም ሊዘጋጅ ነው

በማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ላይ የሚያተኩር የዘጋቢ ፊልም ቀረፃ እንደሚጀመር ይጠበቃል። ዘጋቢ ፊልሙ በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ በማህበራዊ ተጠያቂነት ዙሪያ የባለድረሻ አካላትን እንቅስቃሴ የማያካትት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

በቅርቡ የፕሮጀክት ስምምነት የፈረሙት 19 ፈፃሚ ድርጅቶች በፊልም ቀረፃው ውስጥ እንደሚሳተፉና የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም አፈፃፀምና እያንዳንዱን ሂደት በዘጋቢ ፊልሙ እንደሚካተት ተጠቁሟል።

## Stories from the Field

During a meeting on the Community Score Card, one of the ESAP2 Social Accountability tools, in Ejere Woreda in January, one woman shared an experience that touched our hearts.

The woman explained she isn't always able to wash herself and her clothes because of her low income. Every time she would go to the health center, she noticed that other people with nicer clothes and who did wash themselves would receive health care services quicker than she. As the providers of the health care services used to make her wait every time, she thought this was the norm.

Due to the training and awareness activities by Oromia Self Help Organizations (OSHO) and Women Support Association (WSA), she now knows that she has the exact same rights at that health center as anyone else, regardless of her income.



## Local government and community collect resources to improve services

In DebreMarkos, where the Amhara Development Association is active, education service deficiencies were identified, including the unavailability of latrines, malfunctioning library, shortage of teachers and student books, high-drop-out rate of vulnerable children and so on. The mentioned gaps were identified by citizens, service providers and local government during an interface meeting, and included in the joint service improvement action plans. Now, the DebreMarkos town administration has more than ETB22,000 for the construction of latrines.

## Documentary on Social Accountability

A production team will start filming a documentary from now till the end of the second phase of the Social Accountability program in Ethiopia, October 2015. The documentary film will capture the facilitation of all stakeholders involved in Social Accountability processes throughout the country.

With the recent signing of the final 19 SAIPs, the documentary film will engage with all stages of the Social Accountability projects.

## የገንዘብ ድጋፍና አስተዳደር ወቅታዊ ዳሰሳ

ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 2006 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የኢሳፐ ሥራ አመራር ኤጀንሲ ለ49 የማህበራዊ ተጠያቂነት ፐሮጀክት ፈፃሚ ድርጅቶች ለፕሮግራም ማስፈፀሚያ ይሆን ዘንድ 2,159,009.99 ዶላር ገንዘብ አስተላልፏል። ይህም እስካሁን የተለቀቀውን የገንዘብ መጠን ወደ 5,793,354.25 የአሜሪካን ዶላር ሲያደርሰው ይኸም የጠቅላላ የፕሮግራሙ በጀት 44በመቶ ገደማ ማለት ይሆናል። በተጨማሪም 30 ፈፃሚ ድርጅቶች እስከ ታህሳስ 2006 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ከ2,590,305.49 የአሜሪካ ዶላር የሚሆን ወጪ በአግባቡ አወራርደዋል።

የሥራ አመራር ኤጀንሲው በጥር 2006 ዓ.ም ለ49 የማህበራዊ ተጠያቂነት ፐሮጀክት ፈፃሚ ድርጅቶች የገንዘብ አስተዳደር ማነቃቂያ ሥልጠና በመስጠት ባለፉት ሩብ አመታት የተገኙ ስኬቶችና የሂሳብ ሪፖርትን በወቅቱ በማቅረብም ሆነ ወጥነት ያለው አሰራር በማስፈን ዙሪያ መሻሻል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ተችሏል።



Photo by MA Staff

## የፕሮግራም አፈፃፀም ዳሰሳ

ከጥቅምት እስከ ታህሳስ 2006 ዓ.ም ባሉት ወራት ውስጥ በ15 ወረዳዎች በማህበረሰብ ወኪሎችና ዜጐች፤ ከአገልግሎት ሰጪዎችና የአካባቢ መሥተዳደሮች (በጠቅላላው ወደ 3,820 ተሳታፊዎች ከዚሁም 38 በመቶ የሚሆኑ ሴቶች የተካፈሉበት) የገፅ ለገፅ ውይይቶች ተካሂደዋል። ውይይቶቹም 15 የጋራ የአገልግሎት ማሻሻያ የድርጊት መርሃ ግብሮችን ለመተለም አስችለዋል ።

በትኩረት ቡድኖችና ሌሎች ተመሳሳይ ውይይቶች አማካኝነትም ከ11,500 በላይ የሚሆኑ ዜጐች ጥራት ያለውን አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን እንዲጠይቁ ታግዘዋል።

ዜጐች ጥራት ያለው መሠረታዊ አገልግሎቶችን የማግኘት መብታቸውን፣ተዛማጅ ሀላፊነትና ግዴታቸውን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማሰብ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ፈፃሚ ድርጅቶቹ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ መድረኮችን አዘጋጅተዋል። በዚህም በሶስት ወራት ውስጥ ወደ 26,593 የሚጠጉ ዜጐችን ለመድረስ ተችሏል። ከነኚህም ውስጥ በአብዛኛው ተጋላጭና በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተገለሉ የህብረተሰቡ ክፍሎች ናቸው።

## አዲስ የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያ እናስተዋውቅዎ

የመንግስት ወጪ ዳሰሳ (Public Expenditure Tracking Survey - PETS ) አዲሱ የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያ ነው። ይህ መሳሪያ ለመሠረታዊ አገልግሎት እንዲውል የታቀደን የመንግስት በጀት በአግባቡ ጥራት ያለውን አገልግሎት ለማድረስ መዋሉን ለመከታተል ያስችላል። ዜጐች ይህን መሳሪያ በመጠቀም የመንግስት ወጪ ፍታሃዊነት፣ ግልፅነት ብሎም ተጠያቂነትን እንዲከታተሉ ያስችላቸዋል። PETS የሂሳብ መረጃዎችን ማቅረብ ስለሚያስችል የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የገንዘብና የግብዓት ምንጮችን ለማወቅ ብሎም በአግባቡ ወጪ መደረጋቸውን ለመከታተል ያስችላቸዋል። የዚህን አዲስ መሳሪያ አሠራር በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ካሻዎ ድረ ገጻችንን WWW.Esap2.org.et ይጎብኙ።

## Grants and Financial Management Update

In the period of October-December 2013, the MA has disbursed an additional amount of USD 2,159,009.99 to 49 Social Accountability Implementing Partners (SAIPs), including the new 19 SAIPs for project implementation. This brings the total disbursed amount to USD 5,793,354.28, which is 44% of the overall available program budget. The 30 (first batch) SAIPs have settled a total of US 2,590,305.49 as of December 2013.

The MA provided a financial refresher training course in January 2014, to make financial staff of all 49 SAIPs aware of the successes achieved in the past quarters and to discuss areas that require improvement, such as the consistency in submitting financial reporting.



Photo by MA Staff

## Program Performance Update

Interface meetings between community representatives and service providers, local government officials and citizens have been organized in 15 Woredas (a total of 3,820 participants) between October and December 2013, which resulted in a total of 15 joint service improvement plans. The total number of women represented in these meetings is just under 38%.

Through the Focus Group Discussions and other meetings, more than 11,500 citizen representatives have been assisted to demand access to quality services.

To increase citizens' awareness of their rights, responsibilities and entitlements to the basic services, SAIPs have organized ongoing sensitization workshops and events at Woreda and Kebele level. So far, 26,593 citizens have been reached, from which the majority are vulnerable and socially excluded groups.

## New Social Accountbaility Tool

Public Expenditure Tracking Survey (PETS) is the newest Social Accountability Tool. The tool is used to assess if allocated budget for the provision of basic services is actually spent as intended, to deliver quality services. Citizens can use it to assess equity in public expenditure and to improve transparency and accountability in budget execution. With PETS, financial information can be presented in a way that allows different stakeholders to discuss where money and inputs are coming from and how they are being spent. A guide on this new tool can be found on our Website: www.esap2.org.et

## በኢትዮጵያ እየተተገበረ ስላለው የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር ዶ/ር አብርሃም ተከስተ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

ክቡር ዶ/ር አብርሃም ተከስተ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ናቸው። ሚኒስትር ደኤታው የኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ጥምር ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው ።

ጥያቄ. መንግስት ማህበራዊ ተጠየቂነትን በሰፊው በኢትዮጵያ ለማሥረፅ በፅናት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ምክንያቱ ምንድን ነው ?

መልስ. ማህበራዊ ተጠያቂነት መንግስት መልካም አስተዳደርን ለማሥፈን እያደረገ ያለው ጥረት ዋና አካል ነው ማለት ይቻላል። በአገልግሎት አሠጣጥ ዙሪያ ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማሥፈን በራሱ ትልቅ ጉዳይ ነው። የምንሠጣቸው አገልግሎቶች የሚዳረሱበት ሁኔታ ግልፅ መሆን አለበት። ማን ምን ሊያገኝ እንደሚገባ፣ መሠረታዊ አገልግሎቶች እንዴት መዳረስ እንዳለባቸው የመሣሠሉት ነገሮች ግልፅ ሆነው መቀመጥ አለባቸው። በመሆኑም ተጠያቂነት ማሥፈን የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል።

ጥያቄ. በተደጋጋሚ እርሶ ማህበራዊ ተጠያቂነት የህይወት አካሄድ መሆኑ ሊሠመርበት እንደሚገባ ሲናገሩ ይደመጣል ይህንን ሲሉ ምን ማለትዎ ነው?

መልስ. ማህበራዊ ተጠያቂነት ሲባል የመንግስት ዘርፎችንና የህዝብ አገልግሎቶችን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። በሁሉም ቦታ ሊሰርፅ የሚገባው ከመሆኑም በላይ ሁሌም በተግባር ልናሳየው የሚገባ ጉዳይ ነው። ማህበራዊ ተጠያቂነትን በህይወት አካሄዳችን የምናካትት ከሆነ ተቋማዊና ቀጣይ እንዲሆን በማስቻል ብሎም በሀገሪቱ ውስጥ መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ ይረዳል።

ጥያቄ. በኢትዮጵያ ውስጥ ማህበራዊ ተጠያቂነትን ለማሥረፅ በሚደረገው ጥረት ዙሪያ ያሉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው ?

መልስ. ዋናው ነገር ማህበራዊ ተጠያቂነት መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ለሚደረገው ጥረት ያለውን አይነትኛ ሚና በቅጡ መረዳት ነው። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የተለያዩ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የሚኖሩባት ትልቅ ሀገር ናት። በመርህ ደረጃ ማህበራዊ ተጠያቂነት የትም ሊተገበር የሚችል ጉዳይ ቢሆንም በሁሉም ቦታ ግን በተመሣሣይ መንገድ ይተገበራል ማለት ግን አይቻልም። ስለሆነም ማህበራዊ ተጠያቂነት ተቋማዊ ለማድረግና በበቂ ሁኔታም ለማስረፅ ሲሞከር የየአካባቢውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መሆን አለበት።

## Interview with State Minister H.E. Dr. Abraham Tekeste on Social Accountability in Ethiopia

H.E. Dr. Abraham Tekeste is the State Minister of the Ministry of Finance and Economic Development. He is also the Chairman of Ethiopia's Social Accountability Program Steering Committee.

Q: Why is the government so committed to widely introduce Social Accountability within the Ethiopian society?



Courtesy of MoFED

A: Social Accountability is a central element of our good governance program. Ensuring transparency and accountability in the delivery of public services is an important objective on its own. The services we deliver have to be transparent in how they are delivered, who is entitled to what, how these public services can be accessed and so on. Accountability is central to ensuring a rule of law.

Q: You have repeatedly said that Social Accountability is a way of life. What do you mean by that?

A: Social Accountability is not only about the public sector or public services. It is something we should be able to implement and mainstream everywhere and we should always try to demonstrate in our actions. Once we internalize Social Accountability as our way of life, it becomes institutionalized, sustainable and eventually it leads to the objectives of ensuring good governance in the country.

Q: What are the challenges of mainstreaming Social Accountability in Ethiopia?

A: The most important thing is to really understand the significance of Social Accountability as an instrument of good governance. Ethiopia is a very diverse and big country. In principle, Social Accountability works everywhere but the context is not always the same. So when trying to institutionalize Social Accountability we really need to understand the local context and then experiment its institutionalization accordingly.

ጥያቄ. የሥራ አመራር ኤጀንሲው፣ የፕሮጀክቱ ፈፃሚ ድርጅቶች ብሎም የሚኒስቴር መሥሪያ ቤትዎ በኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ቀጣይነት እንዲኖረው ለማሥቻል ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ይላሉ ?

መልስ. በአሁን ሰዓት 30 የፕሮጀክት ፈፃሚዎች በመጀመሪያው ዙር ሥራ ላይ ገብተው በትግበራ ላይ ይገኛሉ። በሁለተኛው ዙር ደግሞ ተጨማሪ 19 ድርጅቶች ለትግበራ በዝግጅት ላይ ይገኛሉ። ቀዳሚ ሃላፊነታችን የሚሆነው እንግዲህ በተገቢው ሁኔታ ማህበራዊ ተጠያቂነትን መተግበር ነው። ያ ደግሞ ፈፃሚ ድርጅቶችን መደገፍና አቅማቸውን መገንባትም ይጠይቃል። ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ሥርዓትን መዘርጋት ብሎም በፈፃሚ ድርጅቶችና የአካባቢ መንግስት አካላት የእርስ በእርስ መማማርንና ልምድ መለዋወጥንም ይጠይቃል።

ጥያቄ. አንዳንድ ፈፃሚ ድርጅቶች የማህበራዊ ተጠያቂነትን ለማስፈን እያደረጉ ባለው ጥረት ውስጥ ከአካባቢ መሥተዳድሮችና አንዳንድ አገልግሎት ሰጪዎች በኩል ችግር እንደሚገጥማቸው ሲናገሩ ይደመጣል። በዚህ አጋጣሚ ለነዚህ የመስተዳድር አካላትና አገልግሎት ሰጪዎች የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

መልስ. እንደሚመስለኝ የአካባቢ መሥተዳደሮች የማህበራዊ ተጠያቂነት ጥረቱ የተለየ ፕሮግራም ሣይሆን በጠቅላላው በኢትዮጵያ ያለው የመልካም አስደዳደር የማስፈን ጥረት አካል መሆኑን በቅጡ ሊረዱ ይገባል። ሁላችንም የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራሙ ስኬታማ እንዲሆን ሀላፊነት አለብን። ስለሆነም የአካባቢ መሥተዳድሮች ከፈፃሚ ድርጅቶች ጋር በትብብር መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ፈፃሚ ድርጅቶቹም ዜጎች ያላቸውን መብት፤ መብትም ብቻ አይደለም ሃላፊነት ጭምር ለህብረተሰቡም ሆነ ለመስተዳድሩ አካላት በተገቢው መንገድ ግንዝቤ ለማስጨብጥ ጥረት ማድረግ አለባቸው ።

ጥያቄ. ካለፈው ልምድ በመነሣት አንዳንድ ዜጎች የመንግስትን ለጥያቄዎቻቸው ምላሽ የመስጠት ዝግጁነት በጥርጣሬ የሚመለከቱበት ሁኔታ ነው ያለው። እርስዎ ታዲያ የዜጎችን ጥያቄ በተገቢው ከመመለሥ አኳያ የመንግስትን ዝግጁነት እንዴት ይገልፁታል?

**“ መብትን ብቻ ሳይሆን ዜጎች ግዴታቸውንም ልብ ይበሉ! ”**

መልስ. ለማህበራዊ ተጠያቂነትና መልካም አስተዳደርን ለማሥፈን በሚደረገው ጥረት ውስጥ የመንግስት ፅናት ምንም ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚገባው ጉዳይ አይደለም። ያም ሲባል ግን ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ነው ማለት አይደለም፤ ዜጎችም ቢሆኑ እኮ እነዚህን ፈተናዎች ለማለፍ የራሳቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል። ለውጥ ማምጣትም ሆነ ፖሊሲና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ጫና ለማሳደር የሚፈልግ ማንኛውም አካል አስቸጋሪ ድርድሮችን ለማካሄድ መወሰን ይኖርበታል። ማህበረሰቡም ቢሆን በዚህ ረገድ በንቃት መሣተፍ ይጠበቅበታል። መንግስት ብቻውን ግልፅነትና ተጠያቂነትን ማሥፈን አይችልም።

ሙሉውን ቃለ ምልልስ መመልከት ካሻዎ

ድረ ገጻችንን WWW.Esap2.org.etይመልከቱ

Q: How can the Management Agency, the SAIPs and MoFED make Social Accountability sustainable in Ethiopia?

A: The first round of 30 SAIPs are now on the ground implementing Social Accountability. The second round, 19 of them, are about to start Social Accountability programs. Our immediate responsibility is to effectively implement Social Accountability and this requires supporting and capacitating the SAIPs, it requires a very strong Monitoring and Evaluation mechanism, it requires learning and sharing experiences across SAIPs and local authorities.

Q:Some SAIPs face problems with local officials and regional BoFED's when trying to implement Social Accountability projects. What is your message to those local government officials and service providers?

A: I think local authorities need to properly understand that Social Accountability is not a separate program but that it lies at the heart of Ethiopia's good governance program. We all share the responsibility to make sure that Social Accountability is successfully implemented. So local authorities should work closely with SAIPs in implementing Social Accountability. I think the SAIPs have to effectively create awareness among communities and local officials about the rights of citizens and that it's not about rights only, it is also about the responsibilities of citizens.

Q: Some citizens are skeptical about the government's readiness to respond to their demands because of previous experiences. How ready is the government to change their citizen's' demand into supply?

**“ It's not about rights only, it is also about the responsibilities of citizens. ”**

A: There should not be any illusion with regard to our commitment to good governance and Social Accountability. This doesn't mean that everything will be rosy. But citizens have responsibility too in addressing these challenges. For all actors, if you want to make a difference, if you want to influence policy and decision-making, then you should be in for a difficult negotiation. We need communities to be actively engaged. The government cannot ensure transparency and accountability on its own.

Read the full interview with the minister on our Website: www.esap2.org.et

## የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈፃሚ ድርጅቶች በስልጠና ወቅት የአሳታፊ ቪዲዮ ሰሩ

ከ14 የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ፈፃሚ ድርጅቶች የተውጣጡ ተሳታፊዎች ባለፉት ሦስት ወራት በሁለት ዙር በተከናወኑ የአሳታፊ ቪዲዮ ቀረፃ ሥልጠና ተሳታፊ ሆነዋል። የመጀመሪያው ስልጠና በአዲስ አበባ ሁለተኛው ደግሞ በአዳማ ተካሂዷል። የኢሳፕ ስራ አመራር ኤጀንሲ ሦስተኛውን ዙር ሥልጠና በሚቀጥሉት ወራት ለማካሄድ አቅዷል ።

## SAIPs Producing their Own Videos During Training

Participants from 14 different SAIPs were part of the Participatory Video Trainings that was given twice in the past three months.The first training took place in Addis Ababa, the second in Adama. The MA is planning to organize a third training in the coming months.



Photo by MA Staff



Photo by MA Staff

አሳታፊ ዘጋቢ ቪዲዮ አንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን የራሱን የዘጋቢ ፊልም የሚቀርፅበት መንገድ ነው። አሳታፊ ቪዲዮ ሰዎችን የሚያቀራርብ ፣ በተለይም የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ድምፅ እንዲሰማ ፣ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በፊልሙ ቀረፃ ላይ ስለሚሳተፉም በህብረተሰብ መካከል ያሉ ችግሮችም ለመፍታት የሚያስችል ስልት ሲሆን ለዕይታ በሚቀርብበትም ጊዜ ውይይቶች እንዲቀሰቅሱ ለማድረግ የሚያስችል አይነተኛ መንገድ ነው።

Participatory Video is a form of media in which a group or community creates their own film. Participatory Video is also a great way of bringing people together, giving a voice to marginalized groups or individuals and solving problems within communities since everyone is encouraged to be part of the video production. Consequently, the videos are shown in the different communities, sparking debates and discussions.

አሳታፊ ቪዲዮዎች ከባለድርሻ አካላት፣ ማህበረሰብ ቡድኖች፣ ወረዳ መሥተዳድር አካላት፣ የማህበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴ አባላትና ሌሎች አካላት ጋር የሚደረጉ ቃለ ምልልሶችን፣ ውይይቶችንና ክንውኖችን የሚያሣይ መሳሪያ ነው።

አሳታፊ ቪዲዮዎችን ለመመልከት ካሻዎ ድረ ገፃችንን www.youtube.com/esap2 ይጎብኙ

"አሳታፊ ቪዲዮ ባለድርሻ አካላት ስለሚያጋጥማቸው ችግሮች በግልፅ እንዲናገሩ ዕድል ይሰጣቸዋል።

ሰሎሜ ኩምሳ

የአሳታፊ ቪዲዮ ሥልጠና ተሳታፊ



Photo by MA Staff

The videos show interviews, conversations and practices among different Social Accountability stakeholders, from community groups, Woreda officials, Social Accountability committee members and others.

Watch the videos on our Youtube channel: www.youtube.com/esap2

*"Participatory Video will help stakeholders to speak more openly about their problems."*

Solome Kumsa,

Video Training participant:

"በዚህ ቪዲዮ ከቀበሌ፣ ከተማና ክልሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ እንችላለን"

ፀሃይነሽ ቻፋኮ

የማህበረሰብ አባል

*"With these video's we can share our experiences with other kebeles, cities and regions."*

Tsehainesh Chafako,

Community Member:

"ስለአገልግሎቶች ቁጭ ብለን ከምናወራ ይልቅ እንዴት ማሻሻል ይቻላል የሚለውን በቪዲዮ በመስደገፍ ማየት የተሸለ አማራጭ ነው"

ሂርጳዬ ጌዶሴ

የማህበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴ አባል

*"It is better to see in front of you how you can improve services, than to just sit and only talk about it,"*

Hirphae Gaedose,

Social Accountability Committee Member:

Read more on the last page of this newsletter to find out how you or your colleagues can sign up for the next round of Participatory Video Training!

## ሴኬታማው የአዳማ የመማማሪያ መድረክ

በአዳማ በየካቲት ወር ውስጥ ሁለት የልምድ ልውውጥና የመማማሪያ አውደ ጥናቶች ተካሂደው ነበር። በስብሰባው ወደ 350 የሚደርሱ ከ49 ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ፈፃሚ ድርጅቶች፣ ከሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮዎች ከፋይናንስ ግልፅነትና ተጠያቂነት ተወካዮቻቸው፣ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም የልማት አጋሮች ተወካዮች ተሳትፈዋል።

በአዳማ የተደረገው የመማማሪያ መድረክ የተናጠል ክንውኖችን በማነፃፀር የሚካሄድ የልምድ ልውውጥ ሂደት ሲሆን ትኩረቱም በማህበራዊ ተጠያቂነት



Photo by MA Staff

አተገባበር ሂደት ላይ ያሉ ልምዶች ማነፃፀር፣ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን እንዴት በብቃት ማሳተፍ እንደሚቻል፣ ሥርዐተ ፆታን በፕሮጅክት ትግበራ ሂደት ማስረፅንና በተለይም ፈፃሚ ድርጅቶች ዜጐች መንግስትና ባለድርሻ አካላት በማህበራዊ ተጠያቂነት ዙሪያ ያመጡትን የባህሪ ለውጥ ምን ያህል እንዳረካቸው መመዘንና ከተገኙ መሻሻሎች ጋር ማወዳደር ነበር። በእያንዳንዱም ደረጃ ተሳታፊዎች በኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክትና በፋይናንስ ግልፅነት ተጠያቂነት መካከል ያለው መስተጋብር ዙሪያ ውይይት አካሂደዋል።

እነዚህ ንፅፅሮች በተሳታፊዎች መካከል የተለያየ መረዳትና ልምድ እንዳለ የሚያሳዩ የነበረ ሲሆን በተለይም ልዩነት ጎልቶ የታየው የአገልግሎት ሰጪዎች ለዜጎች ምላሽ የመስጠት ሁኔታ ላይ ነበር። እነዚህ ክርክሮች ደግሞ ወደፊት ሊኖሩ ይችላሉ የተባሉ ዜጎች በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያላቸውን እርካታ ወይም አለመርካት መመዘኛ ዘዴዎች ለመፈተሽ ረድቷል።

ተሳታፊዎች በተለይ ደግሞ ስርዓተ ፆታን በፕሮጀክቱ ውስጥ ማስረፅን በተመለከተ በነበረው ውይይት ላይ ንቁ ውይይት ሲያደርጉ ተስተውለዋል። ይህም የሚያሳየው የማህበራዊ ተጠያቂነት ሂደት ሴቶችን ማሳተፍ ብቻ ሳይሆን እንደ ገፅ ለገፅ ውይይቶችና የጋራ የድርጊት መርሃ ግብሮች ሲተገበሩም ሆነ ሲተለሙ ሁለቱም ፆታዎች በአገልግሎት ዙሪያ የሚያነሷቸው ጉዳዮች በእኩልነት እንዲስተናገዱ ማድረግ እንዳለበት ነው። በወቅቱም የሴቶችና የወንዶች የጋራ ጉዳዮች በገፅ ለገፅ ውይይቶችና የጋራ የድርጊት መርሃ ግብሮች ውስጥ እንዴት እንደተካተቱ አክሽን ፎር ዴቬሎፕመንት (AFD) የተሰኘው ፈፃሚ ድርጅት ገለፃ አድርጓል።

ስለሚቀጥለው የመማማሪያ መድረክ አስተያየት ካለዎ በinfo@esap2.org.et ይፃፉልን።

## Succesful First Learning Benchmark Meeting in Adama

Two ESAP2 Learning Benchmark meetings were organized in Adama in February, which were attended by more than 350 representatives of all our 49 Social Accountability Implementation Partners (SAIPs). Additionally, service providers, development partners and government representatives both from MoFED and BoFED regional offices in charge for the Financial Transparency and Accountability (FTA) support program attended the sessions.




Photo by MA Staff

Learning Benchmarkenables sharing experiences by comparing practices.

The Learning Benchmark meetings in Adama especially focused on comparing progress with the Social Accountability process, social inclusion and gender mainstreaming practices SAIP satisfaction with behavioral change of citizens and government stakeholders in the project. At each step of the way, participants discussed opportunities for developing linkages between ESAP and FTA.

The comparison sparked a discussion that showed different experiences, practices and approaches between SAIPs on the responsiveness of service providers. These debates encouraged to further examine mechanisms of evaluating satisfactions and dissatisfaction.

Participants were especially enthusiastic about the gender mainstreaming discussions. These showed that Social Accountability processes should not only emphasis on participation of women, but also in terms of service issues, such as how the needs of both women and men are included in the interface meeting and joint action plans. Some SAIPs, such as Action for Development (AFD), showed how the common need of both women and men has been included during the interface meeting and joint action plans.

Do you have suggestions for the next one? Please email us: info@esap2.org.et

## ጥያቄና መልስ

በየሣምንቱ በፌስ ቡክ ገፃችን ላይ ጥያቄና መልስ ያገኛሉ።

በየሣምንቱ አራት ተመሣሣይ ጥያቄዎች ለተለያዩ የማህበራዊ ተጠያቂነት ባለድርሻ አካላት ማለትም የማህበረሰብ አካላት፣ ፈፃሚ ድርጅቶች፣ የወረዳ መሥተዳደር አካላት እና አገልግሎት ሰጪዎች ይቀርባሉ።

1. ማህበራዊ ተጠያቂነት ለእናንተ ምን ማለት ነው?
2. በማህበራዊ ተጠያቂነት ዙሪያ በጐ ልምድ ካላችሁ ያንን ብታጋሩን
3. በማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም ትግበራ ወቅት ያጋጠሟችሁ ችግሮች ካሉ
4. ማህበራዊ ተጠያቂነት እንዴት ማስረፅ ይቻላል?

የፌስ ቡክ ድረ ገፃችንን www.facebook.com/esap2 በመጎብኘት በዚህ ሳምንት ለነኚህ ጥያቄዎች ማን መልስ እንደሠጠ መልሦቹ ምን እንደሚመሥሉ በመመልከትና ከሌሎች ልምድ በመቅሰም ውይይት ይጀምሩ።

## Question & Answer

Every week you can find a new Q&A on our Facebook page! Q&A stands for Questions & Answers.

The same four questions will be asked every week to different Social Accountability stakeholders, meaning community members, implementation partners, woreda officials, and service providers:

1. What does Social Accountability mean to you?
2. What is your best experience with Social Accountability?
3. What challenges did you face when trying to implement Social Accountability?
4. How can Social Accountability be mainstreamed?

Visit www.facebook.com/esap2 and read who answered this week's Q&A to find out more on other people's experiences with Social Accountability and start the discussion!

ይህ በአለም ባንክ የሚተዳደረው በለጋሾች የአደራ ፈንድ ድጋፍ የሚደረግለት የኢሳፕ2 (ESAP2) የዜና መጽሔት ነው።

This is a quarterly newsletter published by the MA of ESAP2 funded by World Bank administered multi-donor trust fund.

MANAGEMENT AGENCY

GOPA | VNG International | YEM – Consultant Institute

Tel. +251-11-6634661, 6634601
Cape Verde st. | P. O. Box 28024/1000
WMA Sets Bldg, 2nd Floor | Addis Ababa, Ethiopia
info@esap2.org.et | Facebook: ESAP2





## ከኢሳፕ2 ዲጂታል አለም

## From ESAP2 Digital World

የአሳታፊ ቪዲዮ ቀረፃ ፕሮግራም ላይ መሳተፍ ይቻል ይሆን ?

እንዳለው።

ውድ እንዳለው

ሌላ የሥልጠና ፕሮግራም ለማዘጋጀት እናሰባለን ማለትም የፈፃሚ ድርጅቶች ፍላጐት ካለ። ድርጅታችሁ ለመሠልጠን ፍላጐትና አስተያየት ካለው ያንን በmarijke.bos@esap2.org.et ላክልን።

ሃይ MA team አዳማ ለተደረገልን ሁሉ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ። ነገር ግን እስካሁን በጅዳ ወረዳ የገጠር ውሃ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን ለማግኘት አልቻልኩም። ከወረዳዎች እስከ ክልል ቢሮዎች ድረስ በየትኛው በኩል የአገልግሎት ደረጃዎችን ማግኘት እንደምችል ተቸግሪያለሁ። አመሰግናለሁ።

የማነ ነኝ

ውድ የማነ

የአገልግሎት ደረጃዎች (Standards) ከክልል ክልል ይለያያሉ ስለሆነም ዜጐች በአካበቢው ያለውን የአገልግሎት ደረጃታሳቢ ባደረገ መልኩ አገልግሎት እንዲደርሳቸው ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።በወረዳውያሉPublic Finance Management/Financial Transparency and Accountability ሃላፊዎች የአገልግሎት ደረጃ ሊሰጡህ ይገባል። ካልሆነ ግን የክልሉን የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ና የውሃና ፍሳሽ ቢሮዎች እንዲረዱህ መጠየቅ ትችላለህ። የብሄራዊ የውሃ አገልግሎት ደረጃ የ 2006ቱን አለም አቀፍ የውሃ ተደራሽነት ዕቅድ በመመስረት ያወጣው ደረጃ ግን ለገጠራማ አካባቢዎች በቀን 15 ሊትር በነፍስ ወከፍ በ1.5 ኪሜ አማካይ ርቀት ውስጥ ሲሆን በከተማ በቀን 20 ሊትር በነፍስ ወከፍ በ0.5 ኪሜ አማካይ ርቀትመሆኑን ያስቀምጣል።

Is it possible to join the Participatory Video Training?

Endalew

Dear Endalew,

We will consider organizing another round of training, if SAIPs are interested. Kindly send an explanatory email to marijke.bos@esap2.org.et, if you want your organization to be trained on Participatory Video.

ESAP2

Hi MA, Thanks for everything in Adama. But I still cannot access "water service standard" of water service delivery for rural areas in Jidda woreda. I wonder where I can get information about water standards, at all levels, from woreda to the government.
Thanks, Yemane

Dear Yemane,

Standards for services may vary from region to region, so it is important that citizens are supported to get the local standards for services in their Woreda. The FTA or PFM officer at your Woreda should be able to help you access the standards, if not contact the regional BoFEDs for help.The national standard for the water sector from the Universal Access Plan 2006 is: 15liter/capita/day for rural setting with a 1.5km service radius. For urban settings, the standard is 20liter/capita/day with a 0.5km service radius.

ESAP2

Reha Touch: 091-120 9525